# የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ)
# UNITED ETHIOPIAN DEMOCRATIC FORCES (UEDF)

## የኢትዮጵያና የአካባቢው ሕዝብ የፍትኅ ትግል አወንታዊ ምላሽ የሚያገኘው ከኢሕአዴግና ከሻዕቢያ ፀረ ሕዝቦች ባሻገር ማየትና ማሰብ ሲቻል ብቻ ነው!

የሻዕቢያና የኢሕአዴግ አመራሮች በሚያስታጥቋቸው ኃይሎች አማካይነት አካባቢያችንን ከማድማት አልፈው በቀጥታ ወደ አውዳሚ ጦርነት የሚያመሩበት አደጋ እየተከሰተ መሆኑን ከየአቅጣጫው የሚወጡ ዘገባዎች እያስጠነቀቁ ይገኛሉ:: ይኽ ጦርነት ሁለቱ ፀረ ሕዝብ ኃይሎች ለኅልውናችን ያስፈልገናል በሚል ሳቢያ የሚቀሰቅሱት ጦርነት እንጂ ሰላም፥ እፎይታ፥ ዴሞክራሲ፥ ፍትኅና እድገት ከሰማይ በላይ ርቆበት ያለው የአካባቢው ሕዝብ የሚጠይቀውም የሚመኘውም አይደለም:: ሕዝባችንን በሽብር አገዛዝ አፍነው ይዘው የሚገኙት የሕወሓት/ኢሕአዴግ መሪዎች ይኽንን አፍጥጦ የመጣሜጦርነት የኢትዮጵያን ጥቅም ለማስከበር በሚል ሽፋን ሊያቀርቡልን እንደሚሞክሩና በዚህም የኢትዮጵያን ሕዝብ ድጋፍ ማግኘት ይቻላል የሚል የተሳሳተ ስሌት እንዳላቸው ሳይታለም የተፈታ ጉዳይ ነው:: የሻዕቢያ መሪዎችም በበኩላቸው ሕዝባችንም ሆነ የኢትዮጵያ ዴሞክራቶችና አገር-ወዳድ ኃይሎች በጭፍን የኢሕአዴግ ጥላቻ ተመርተው ከጎናችን በመቆም ከጎናችን ይቆማሉ የሚል አደገኛ ስሌት ላይ እንዳሉ ግልፅ ነው::

ሕዝባችን ከኢሕአዴግ መሪዎች ጋር ያለው ጠብ መነሾው ለምን ለአገር ጥቅም፥ ክብርና የግዛት አንድነት ቆማችሁ የሚል አይደለም:: የአልጀርስ ስምምነት በተባለ ፀረ ኢትዮጵያ ሰነድ ለምን የኢትዮጵያን ክብር፥ ጥቅምና የግዛት አንድነት አሳልፋችሁ ሰጣችሁ? ለምን ድንበር ኮሚሽን በተባለው ፀረ ኢትዮጵያ አካል አማካኝነት አገራችን ሞተው በተቀበሩ በቅኝ ግዛት ውሎች ትዳኝ ብላችሁ ተስማማችሁ? ለምን በዚህ ከጥንስሱ ሕገ-ወጥ በሆነ መድረክ ፊት እንኳን ቢሆን ከአገራችን ጥቅም አንፃር ሳይሆን ሽንጣችሁን ገትራችሁ የኢትዮጵያን ጥቅም ስትሞግቱና አሳልፋችሁ ለሽዕቢያ ስትሰጡ ተስተዋላችሁ የሚል ተቃውሞ ነው::

ወደ ዳግም አውዳሚ ጦርነት እየመራን ያለው ቀውስ የተጀመረው ዓይን ባወጣ ሁኔታ የሻዕቢያ መሪዎች ምን ጊዜም የኢትዮጵያ የነበሩና አሁንም የሆኑ ግዛቶችን በማንኛውም መስፈርት የዓለም-አቀፍ ሕግጋትን በጣሰ አካሄድ ወርረው በመያዛቸው ነበር:: በወቅቱ ይኽንን በግልፅ የተረዳው ዓለም-አቀፉ ኅብረተሰብ በተለይ በአፍሪቃ አንድነት ድርጅት አነሳሽነት በቀረበው የመፍትኄ ሀሳብ ላይ በመመርኮዝ ሻዕቢያ ወራሪ ጦሩን አውጥቶ ከግንቦት 1990 በፊት ወደ ነበረበት ቦታ እንዲመለስ እንደጠየቀና ይህንንም ሀሳብ የተባበሩት መንግሥታት የፀጥታ ምክር ቤትም ሆነ የተለያዩ መንግሥታት ደግፈው ተንቀሳቅሰው እንደነበረ ይታወሳል:: ሆኖም ዓለም-አቀፉ ኅብረተሰብ ይኽን ወረራ ከአንገት በላይ በሚመስል መልክ ከመኮነን አልፎ ሻዕቢያ ይኽንን ሀሳብ እንዲቀበል ጫና ሊሆን የሚችል ምንም እርምጃ አልወሰደም:: በዚህ ሁኔታ በተቀሰቀሰው ጦርነት ሳቢያ እስከ መቶ ሺ የሚደረሱ የኢትዮጵያውያንና የኤርትራውያን ወጣቶች ደም ፈስሶ ወራሪው ኃይል ድል ተመትቶ የያዛቸውን ቦታዎች ለቅቆ እንዲወጣ ተገደደ::

አዲስ አበባንና አሥመራን የተቆጣጠሩት ሁለት ፀረ-ሕዝብ ቡድኖች ከመድረኩ በሕዝብ ትግል ተወግደው ነፃ ፍላጎቱን መግለጽ ሳይችል አግባብ ባልሆነ መንገድ እንዲለይ

ዋና መሥሪያ ቤት (Main Office)
ፖ.ሣ.ቁ./P.O.Box 73246
Washington DC 20056-3246, U.S.A
ስልክ/Tel. 202-291-4217 (Fax) 202-291-7645

አውሮጳ (Europe)
Jonathan Str. 82
2524 JJ The Hague, Netherlands
Tel/Fax 31 70 394 6132

የተገደደው ወንማማች የሆነው የኢትዮጵያና የኤርትራ ሕዝብ በሰከነ ውይይት ስለ ወደፊቱ እጣ ፈንታው የሚወስንበት ዴሞክራሲያዊ ሁኔታ እስኪመጣ ድረስ ነገሩ ለጊዜውም ቢሆን እዚህ ላይ መቆም ነበረበት። ይኸ አልሆነም። በአንዳንድ የሕወሓት/ኢሕአዴግ መሪዎች አሻጥርና በዓለም-አቀፍ ኅብረተሰቡ ግፊት ጨርሶ ከመደቆስ የተረፈው ሻዕቢያ በእብሪትና በጦር ሜዳ ያልቻለውን በሽምግልና ሂደት እንዲያገኝ በተጠነሰሰ ሴራ "የአልጀርስ ስምምነት" የተባለ ፀረ ኢትዮጵያ ሰነድ ተፈረመ። ይኸ "ይግባኝ የሌለው ውሳኔ" ይሰጣል የሚል "የድንበር ኮሚሽን" የተሰየመበት ስምምነት የአገራችንን ሕጋዊ መብት ጨርሶ የማያስከብር፥ ምንም ፍትኅዊነት የሌለው፥ ሰላምንም ጨርሶ ሊያመጣ የማይችል ፀረ-ኢትዮጵያ ሰነድ በመሆኑ ከኢሕአዴግ ከራሱም የተወሰኑ መሪዎችን ጨምሮ ዴሞክራቶችና አገር-ወዳድ ኃይሎች ዳር አስከዳር ተቃወሙት። ለምን?

1. የኢሕአዴግ መሪዎች ከቪየና ስምምነት (Vienna Convention) ም ሆነ ከሌሎች ዓለም-አቀፍ የውሎች ሕግጋት አንፃር ሞተው በተቀበሩ የቅኝ ግዛት ውሎች " እንዳኝ" ሲሉ የአገራችንን መብትና ጥቅም ለማስከበር እንዳልተነሱ ገና ከመጀመሪው ግልፅ ነበር። እነዚህ ግዛቶችን ከኢትዮጵያ እየቆረሱ ለቅኝ ገዥዎች ያስረከቡ ውሎች በዓለም አቀፍ የውሎች ሕግ መሠረት በግዴታ የተፈረሙ በመሆናቸው አስገዳጅነት የላቸውም። በሌላ በኩል ደግሞ ዓለም-አቀፍ የውሎች ሕግጋት መሠረት እነዚህን ውሎች አንዱ ተስማሚ ወገን በአንድዮሽ እርምጃ ካፈረሳቸው በሌላው ወገን ላይ አስገዳጅነት የላቸውም። ፋሽሽት ጣሊያን በ1928 ዓ.ም. አገራችንን ወርራ እነዚህን ድንበሮች ሁሉ አፈራርሳ "የጣሊያን ምሥራቅ አፍሪቃ" ብላ ስታቋቁም ያከተመላቸው ናቸው። ሦስተኛ ከሁለተኛው ዓለም ጦርነት በኋላ ጣሊያን ተሸንፋ በሁለቱ አገሮች መካከል የሰላም ውል ሲፈረምና የጣሊያን አገዛዝ ሲከስም እነሱም አብረው ከስመዋል። ስለነዚህ የቅኝ ግዛት ውሎች ሞቶ መቀበር ምክንያትና ሂደት በርካታ ምሁራን በሰፊው የተቹበት ስለሆነ ከዚህ አልፈን ብዙም ሀተታ ውስጥ መግባት የሚያስፈልግ አይመስለንም። ለዚያውም እንግዲህ የኢሕአዴግ መሪዎች በተስፋፊዋ በጣሊያንና በኢትዮጵያ መኻል ከተፈረሙት በርካታና ሙታን ውሎች መኻከል አስገራሚ በሆነ ሁኔታ "እንዳኝባቸው" ያሉት የ1900፥ የ1902 እና የ1908 ፀረ-ኢትዮጵያዊነታቸው ጎልቶ የሚታየውን ሦስት ውሎች ብቻ መርጠው እንደሆነ እናያለን ። ሌላው ቢቀር "የቅኝ ግዛት ውሎች" ከተባለ አይቀር በአንቀፅ 5 ላይ " ጣሊያን በሆነ ምክንያት በፈቃዷ ማንኛውንም ግዛት ከለቀቀች እነዚህን ግዛቶች <u>ለኢትዮጵያ ትመልሳለች"</u> የሚለው በአድዋ ድል ማግስት የተፈረመው መሠረታዊ የሆነው የጥቅምት 1891 ዓ.ም. የአዲስ አበባ ስምምነት ሆን ተብሎ ወደ ጎን ተትቷል።

2. ለዚያውም እንግዲህ ቀኝና ግራውን ሳያይ በእነዚህ ውሎች ብቻ ተመስርቶ ብይኑን እንዲሰጥ የተፈቀደለት የድንበር ኮሚሽን ይኸን በተግባር ከማዋል ይልቅ በእነዚህ ውሎች እንኳን የኢትዮጵያ ናቸው የተባሉትን ግዛቶች በኢሕአዴግ መሪዎች ተባባሪነትና ግፊት ለሻዕቢያ ሲያስረክብ ተስተውሏል። በፀሮናና አካባቢዋ ጉዳይ ብንሄድ ለምሳሌ ኮሚሽኑ "በ1900 ውልና ባሉት መረጃዎች መሠረት" ፀሮናና አካባቢዋ የኢትዮጵያ መሆናቸው እተረጋገጠ እያለ በብያኔው ግን ይኸ አካባቢ ለኤርትራ ተሰጥቷል። ይኸ የሆነበት ምክንያት የኢሕአዴግ መሪዎች እነ ፀሮናን "ያለ ጥርጥር የኤርትራ ግዛቶች ናቸው" ብለው በፅሑፍ ጥያቄ በማቅረባቸው እንደሆነ የኮሚሽኑ ዘገባ (ሪፖርት) ሲያስረዳ፤ "ፀሮናን በተመለከተ ኮሚሽኑ በኢትዮጵያ በኩል በመንግሥት ደረጃ በፅሑፍ የቀረበለለትን ጥያቄ ላለማስተናገድ ስለማይችል በውሉ ላይ ያለውን ድንበር አስተካክሎ ፀሮናን ኤርትራ ውስጥ ለማስቀመጥ አስፈላጊ ሆኖ አግኝቶታል" ይላል። (4/70) ከነ ፀሮና ወረድ ብለን በምሥራቁ ክፍል በቡሬ ጉዳይ የሆነውን ስንመለከት እዚህም ላይ ኮሚሽኑ "ለየት ያለ ሁኔታ" እንዲጋጠመውና የኢሕአዴግና የሻዕቢያ መሪዎች በኅዳር ወር 1991 ዓ.ም. ባደረጉት ስምምነት የዚህን ክፍል ድንበር የሚያካልለውን የ1908 ቱ ውል አፍርሰው በኢትዮጵያ ግዛት የምትገኘውን ቡሬን እንዴት የድንበር ከተማ እንዳደረጓት ይገልጽና በዚህም መሠረት የድንበር ማካለሉ ሂደት በ1908ቱ ውል ሳይሆን በወያኔና ሻዕቢያ ስምምነት መሠረት በኢትዮጵያ ኪሳራ እንደተፈፀመ ያስረዳል። (6/30-6/31)

3. እንግዲህ ሁለቱ ወገኖች እነዚህን ውሎች ሲያስፈልጋቸውና ዓይናቸውን ሳያሹ በዚህ መልክ በኢትዮጵያ ኪሳራ ያስተካክሏቸው እንጂ ኮሚሽኑ ከነሱ ወጣ ብሎ " ፍትኃዊና ርዕቱአዊ እንዲሁም ዘላቂ ሰላምን ሊያመጣ የሚችለው መፍትኄ ይኸ ነው" ብሎ ውሳኔ እንዳይሰጥ እጅ ተወርች የታሰረ አካል እንደሆነ እናያለን። በአልጀርስ ስምምነት አንቀፅ 4/2 መሠረት ኮሚሽኑ "ኤክዜኮ ኤ ቦኖ በሚለው መርኅ መሠረት የመወሰን ሥልጣን የለውም" ተብሎ ተደንግጓል። ይኸ የሕግ ቋንቋ በግልፅ ሲተረጎም "ኮሚሽኑ ርቱዓዊና በጎ ውጤት ሊያመጣ ይችላል በሚል ስሌት ተነስቶ ውሳኔ የመስጠት ሥልጣን አይኖረውም" ማለት ነው። የኢሕአዴግና የሻዕቢያ መሪዎች የኮሚሽኑን አሠራር በዚህ መልክ የቀለፉበት ምክንያት ግልፅ ነው። ፍትኃዊ የሆነ፥ ሰላምን ሊያመጣ የሚችል፥ የሕዝብን ፍላጎት ከቁጥር የሚያስገባ ዴሞክራሲያዊ ውሳኔ ቢባል ኖሮ የጣሊያንን ቅኝ ግዛት ዘመን ጨምሮ ዘለዓለማቸውን ኢትዮጵያን የሆኑና የሻዕቢያን ወረራ ለመመከት መስዋእትነት የከፈሉ ዜጎች ፈቃዳቸው ሳይጠየቅ "ከዛሬ ጀምሮ የኢትዮጵያዊነት ዜግነታችሁ ተገፎ ኤርትራውያን ተብላችኋል" የሚል ኢ-ፍትኃዊ ውሳኔ ማስተላለፍ የሚታሰብ አልነበረም። እንዲህ ዓይነቱ አሠራር በሕዝብና በዜግነት መብቶች አንፃር የሃያኛው ክፍለ ዘመን መሠረታዊ ግኝቶች በተለይም ደግሞ በታኅሣሥ 1959 ዓ.ም. በተፈረመው የዜግነትና የፖለቲካ መብቶች ዓለም-አቀፍ ስምምነት "ሁሉም ሕዝቦች የራሳቸውን ዕድል በራሳቸው የመወሰን መብት አላቸው... " የሚለውና ከዚያም ቀደም ብሎ በሰብአዊ መብት ዓለም አቀፍ ድንጋጌ አንቀፅ 13 "ማንም ሰው በሕገ-ወጥ መንገድና በዘፈቀደ ዜግነቱን አይነጠቅም" የሚሉትን ዓለም-አቀፋዊ እሴቶች የሚጥስ ብቻ አይደለም። በአፍሪቃ ቅርጫ ዘመን ግፈኛ ቅኝ ገዥዎች በበርሊን የ1884 ስምምነት መሠረት በዘፈቀደ አሠራር ከዛሬ ጀምሮ አንተ ኮንጎ፥ አንተ ዩጋንዳ፥ አንተ ናይጄሪያ፥ አንተ ካሜሩን .... እያሉ ሕዝቦችን ብቻ ሳይሆን ቤተሰቦችን ሳይቀር በርሊን በተነደፈ ካርታ እንደታቀረጡ ይታወሳል። ይኸ የአልጀርስ ስምምነት ሂደት የኢትዮጵያ ሕዝብ ከመቶ ዓመት በላይ ወደ ኋላ እንዲመለስ ተደርጎ ልክ እንደ አፍሪቃው ቅርጫ ዘመን ከሔግ በተደረጉ " የድንበር ማካለል ውሳኔዎች" የሕዝቦችን ፈቃድ ከመጤፍ ባልቆጠረ ሁኔታ ኢትዮጵያውያን "ከዛሬ ጀምሮ ኤርትራውያን ተብላችኋል" እየተባሉ የዜግነት መብታቸው ሊሰረዝ የተሞከረበት ዘግናኝና ግፈኛ አካሄድ ነው።

በመሆኑም የኢትዮጵያ ዴሞክራቶችና አገር-ወዳድ ኃይሎች መጀመሪያውኑ በሻዕቢያ ተፈፅሞ የነበረውን ወረራ እንዳወገዙትና ከዚያም የአልጀርሱን ስምምነትም ሆነ የድንበር ኮሚሽኑን ውሳኔ እንደተቃወሙት ሁሉ አሁንም ከዚህ የተለየ አቋም ሊኖራቸው አይችልም። የሻዕቢያ መሪዎች የኢትዮጵያ ሕዝብ ከዳር እስከዳር ያወገዘውን የአልጀርስ ስምምነትና የድንበር ኮሚሽኑን ውሳኔ ተመርኩዘው እንደገና ወረራ ቢጀምሩ ይኸንን ፀረ-ኢትዮጵያ ድርጊት በተገቢ ፀረ-ኢሕአዴግ ተቃውሞው ታውሮ እንደማይደግፋቸው ጠንቅቀው ሊያውቁት ይገባል። የኢሕአዴግ መሪዎችም የባዕዳን ተልዕኮ ለማስፈፀምም ሆነ የራሳቸውን ፀረ-ሻዕቢያ ዓላማ ተግባራዊ ለማድረግ ሕዝባችንን ወደ አውዳሚ እልቂት ለመግፋት ከሞከሩ እንዲህ ዓይነቱን እብደት የኢትዮጵያ ሕዝብ የመረረ ተቃውሞ እንደሚጠብቀው ከወዲሁ ሊያቁት ይገባል እንላለን። ባለፈው ጦርነት ከ100 ሽህ በላይ ለሆኑ ወገኖቻችንን ሕይወት መጥፋት፥ ለብዙዎች አካለ ጎዶሎ መሆንና ለበርካታዎች አለመጠጊያ መቅረት ዛሬም ተጠያቂ ሊሆኑ የሚችሉት የሻዕቢያና የኢሕአዴግ አመራሮች ናቸው። ይኸ ስለተባለ ከድንበር ጥያቄ ዘልቆ የሚሄደውና በሁለቱ ፀረ-ሕዝብ አገዛዞች ሴራ የተፈጠረው በኢትዮጵያና በኤርትራ መካከል ያለው የተወሳሰበ ችግር መፈታት የለበትም ማለት አይደለም። ከፍ ብለን እንዳልነው ይኸ ችግሩን በፈጠሩትና እንዲቀጥልም በሚፈልጉት ሁለት ፀረ-ሕዝብ ቡድኖች የሚፈታ ጉዳይ አይደለም። ከዚህ ይልቅ በሕዝቦች የተባበረ ትግል ሁለቱ ፀረ-ሕዝብ ቡድኖች ተወግደው ዴሞክራሲ በሰፈነበት ሁኔታ በወንድማማችነት መንፈስ በሚካሄድ ውይይት ለመፍታት ሁኔታዎችን ማመቻቸት ያስፈልጋል። ይኸ ደግሞ በጠቅላላ አካባቢው ሕዝቦች እፎይታ አግኝተው አዲስ የሰላምና የብልጽግና ኑሮ እንዲጀምሩ የሚደረግ ትግል ስለሆነ የኢትዮጵያ ዴሞክራቶችና አገር-ወዳድ ኃይሎች ጉዳይ ብቻ አይደለም። በአሁኑ ወቅት ሁለቱ የጥፋት ኃይሎች ለራሳቸው

ጎልውና ያስፈልገናል በሚል ስሌት ብቻ ሳይሆን የሩቅና የቅርብ አሳዳሪ የሆኗቸውን ባዕዳን ተልእኮ ለማራመድ በሱማሊያ ወገን ለይተው ወንድም የሆነውን የሱማሊያ ሕዝብ በአሥራ-አምስት ዓመት የእርስ በእርስ ጦርነት እንኳን ባልታየ ሁኔታ የሞት፥ የስደት፥ የረሃብና የኑሮ መመሳቀል ፈተና እንዲወርድበት እያደረጉ እንደሆነ እናያለን። ሁለቱም ወገኖች በሁለቱም አገዛዞች ውስጥ አለመረጋጋትን ለመፍጠርና ከቻሉም በአዲስ አበባና በአሥመራ ተጠሪ የሚሆኗቸውን አገዛዞች ለመትከል አካባቢውን በሚያስታጥቋቸው ኃይሎች እያደሙ እንደሆነ እናያለን።

በዚህ መልክ የአፍሪቃን ቀንድ በመደቆስ ያለው ቀውስ የዚህ ወይም የዚያ ሕዝብ ሳይሆን የእነዚህ ሁለት አገዛዞች ሰላባ የሆኑትን የአካባቢውን ሕዝቦች በሙሉ የሚዳስስ አጠቃላይ ቀውስ ነው። በመሆኑም የኢትዮጵያ፥ የኤርትራና የሱማሊያ ዴሞክራቶችና የሰላም ኃይሎች ሁሉም በጋራ ሆነው በሁሉም ቦታ ያሉትን ፀረ-ሰላምና ፀረ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች በቁርጠኛነትና በጋራ ለመቋቋም መነሳት ይኖርባቸዋል። ይኸንንም ለማድረግ መንደርደሪያ ሊሆኗቸው የሚችሉትን የጋራ አቋሞች ለመንደፍ በአስቸኳይ ተገናኝተው መወያየት ይጠበቅባቸዋል። በበኩላችን ለዚህ ውይይት መነሻ ሊሆኑ ከሚችሉት ነጥቦች አንዳንዶቹን ብናቀርብ፤

1ኛ. በያለበት ያሉት ፀረ-ሕዝብና ፀረ-ሰላም ኃይሎች እንደሆኑ ጠንቅቶ በመረዳት "በሻዕቢያ እርዳታ ወያኔን ተዋግተን ወይም በወያኔ እገዛ ሻዕቢያን ታግለን... " የሚለው የአንዳንድ ተቃዋሚዎች ስሌት የሕዝቦቻችንን የመከራ ዘመን የሚያራዝም እንጂ ምንም ዘላቂ ሰላም ሊያመጣ እንደማይችል በመገንዘብ ሁለቱን ጦረኞች በአንድ ድምፅ ማውገዝና በጋራ መታገል አስፈላጊነት፥

2. ወንድማማች የሆኑትና በሺህ የታሪክ፥ የፖለቲካ፥ የባህል፥ የኢኮኖሚና ሌሎች ድሮች የተሳሰሩት የኢትዮጵያና የኤርትራ ሕዝብ በረጋና በዴሞክራሲ ሁኔታ ችግራቸውን ፈትተው ስለጋራ ልማትና እጣ ፈንታ ዘላቂ መፍትኄ ሊሰጡ የሚችሉት እነዚህ ሁለት የጥፋት ኃይሎች ከፖለቲካው መድረክ በሕዝብ ትግል ሲወገዱና በኤርትራም በኢትዮጵያም በዴሞክራሲና በብሔራዊ እርቅ መንፈስ የተረጋጋ ኅብረተሰብ ሲፈጥሩ ብቻ ስለሆነ ለዚህ የሚደረገውን ትግል የማስተባበር አስፈላጊነት፥

3ኛ የሱማሊያ ችግር በማንም ጣልቃ ገብነት ሳይሆን በዚያው በሱማሊያ ሕዝብ ጥረት ብቻ የሚፈታ እንደሆነ በመረዳትና በአንድ በኩል የኢሕአዴግ ጦር ጣልቃ-ገብ ወረራና በሌላ በኩል ደግሞ የሻዕቢያ ጣልቃ ገብነት የዚህን ሕዝብ መከራ የሚያባብስ ሁኔታ በመፍጠሩ የሁለቱን ወገኖች ፀረ-ሕዝብ አካሄድ የማውገዝ አስፈላጊነት፥

4ኛ የኢሕአዴግ ጣልቃ-ገብ ወረራ የኢትዮጵያ ሕዝብ ያልመከረበት፥ ያልፈቀደውና የአሸባሪው አገዛዝ ብቸኛ ውሳኔ መሆኑ እየታወቀ የሱማሊያ የሙስሊም ፍርድ ቤቶች መሪዎች በሽብር ተይዛ በመሰቃየት ላይ ባለችው አገራችን ላይ የአወጁት ጂሃድ ጨርሶ ፍትኀዊነት የጎደለው፥ የኢሕአዴግ ሰለባ በሆነው ሕዝባችን ላይ የተቃጣ፥ በውጤቱም በሕዝቦች መካከል ሊዳብር የሚገባውን የወንድማማችነትና የትግግዝ መንፈስ አውድሞ ቀጥታ ለኢሕአዴግ መሪዎች የማገዝ ያህል ስለሚሆን የሱማሊያ ዴሞክራቶች ይኸንን በግልፅ አውግዘው የመውጣታቸው አስፈላጊነት ይገኙበታል።

በእነዚህና በሌሎችም የጋራ በሆኑ ጉዳዮች ዴሞክራቶች ሁሉ እንዲወያዩና በአሁኑ ወቅት በሱማሊያ በመካሄድ ላይ ያለውም ሆነ በሻዕቢያና በኢሕአዴግ መሪዎች እየተደገሰ ያለው የእልቂት ዙር ከአካባቢው ሕዝቦች ጥቅም፥ ሰላም፥ ወንድማማችነትና የእድገት እርምጃ ጋር ምንም ግንኙነት እንደሌለው፥ የአካባባው ሕዝቦች ከዚህ እልቂት ከደም፥ ከእንባና ከጋራ ውድመት ሌላ ምንም እንደማያገኙ ግልፅ በሆነበት ሁኔታ የአካባቢው ዴሞክራቶችና የሰለም ኃይሎች በአንድነት ቆመው መታየታቸው ሊያስገኝ የሚችለውን የፖለቲካና የዲፕሎማሲያዊ እመርታ ተገንዘበው ለዚህ የሰላም ጥሪያችን አዎንታዊ መልስ እንዲሰጡ ጥሪያችንንን እናስተላልፍላቸዋለን።

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት
ታኅሣስ ፪ ሽህ ዓ/ም